Hamlin Fistula Ethiopia

# ሐምሊን ዜና መጽሔት

ቁጥር 6 ፤ ነሐሴ 2010 ዓ.ም.

በሐምሊን ፌስቱላ ኢትዮጵያ በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለሠራተኞቹ የሚሰራጭ

## የሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ
## 8ተኛ ዙር የተማሪዎች ምረቃ እና 10ኛ ዓመት የኮሌጁ ምስረታ



በውስጥ ገፆች


- የተማሪዎች ምረቃ እና የኮሌጅ ምስረታ ክብረ-በዓል 2
- 2010 ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ 4
- የሐምሊን ሚድዋይፎች አሉምናይ ኔትዎርክ 6
- ዓለም አቀፍ ፓርትነርስ ስብሰባ 8
- ከጎበኙን እንግዶች አንደበት 9
- ችግኝ ተከላ በደስታ መንደር 10

# ሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ ተማሪዎቹን ለስምንተኛ ጊዜ አስመረቀ
## •ኮሌጁ 10ኛ ዓመት የምስረታ ክብረ-በዓሉንም አክብሯል



ቅዳሜ ሐምሌ 8፤ 2010 ዓ.ም ጦርኃይሎች አካባቢ በሚገኘው የመኮንኖች ክበብ አዳራሽ በተካሄደው የምረቃና የ10ኛ ዓመት ክብረ-በዓል 20 በሙያቸው የላቁ ሚድዋይፎች ቤተሰቦቻቸው፣ወዳጅ ዘመዶቻቸው እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ተመርቀዋል፡፡ ይህን ተከትሎም ኮሌጁ ከምስረታ አንስቶ እስካሁን ያስመረቃቸው የሚድዋይፈሪ ባለሙያዎች ቁጥር 145 አድርሷል፡፡

በዝግጅቱ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኮሌጁ ዲን አቶ ዘላለም በለጠ ተመራቂዎቹንና ቤተሰቦቻቸውን እንኳን ደስ ያላችሁ ካሉ በኃላ የሰለጠናችሁበት ሙያ ልዩና ከፍ ያለ ትጋትን የሚጠይቅ፣ በአንድ ጊዜ ሁለት ክቡር የሰው ህይወት የማዳን ጉዳይ በመሆኑ በየተመደባችሁበት ቦታ ከምቾታችሁ በላይ ሙያችሁን በማስቀደም የሐምሊን ተማሪዎች የሚታወቁበትን ጥራት ያለው አገልግሎት እንደምታስቀጥሉ እምነቴ ነው ብለዋል፡፡ አቶ ዘላለም አክለውም የ 8ተኛው ዙር የምረቃ ስነ-ስርዓት የሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ 10ኛ ዓመት ክብረ-በዓል ጋር በጥምረት መካሄዱ ልዩ እንደሚያደርገው ተናግረው ተመራቂዎች ላሳደጋቸው ማህበረሰብ የሚሰጡት ግልጋሎት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሐምሊን

ድጋፍ ሁልጊዜም እንደማይለያቸው አረጋግጠውላቸዋል፡፡

ተመራቂና የተማሪዎች ተወካይ የሆነችው ብርቄ ጌታቸው ባደረገችው ንግግር “የምንወድሽ እናታችን እማዬ፣ የረጅም ጊዜ ህልምሽ እውን ሆኗል፡፡ ጥሩ ሚድዋይፎች ሆነን ተመርቀናል፡፡ እድሜሽን ሙሉ የሰጠሽለትን የወሊድ ጉዳቶችን የማከምና መከላከል ስራን ለማስቀጠል ከመቼውም ጊዜ በላይ ተዘጋጅተናል፡፡ የላቀ ክህሎት እንዲኖረን በኮሌጁ ለተደረገልን የተሟላ ድጋፍም እናመሰግናለን” ብላለች፡፡

በምረቃ ስነ-ስርዓቱ ላይ የሐምሊን ፌስቱላ ኢትዮጵያ ተጠባባቂ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ ማሞ፣ የሐምሊን ፌስቱላ ኢትዮጵያ የቦርድ አባል ዶ/ር መንግስቱ አስናቁ፣ በኢትዮጵያ የአውስትራሊያ አምባሳደር ማርክ ሶወርስ እና የካትሪን ሐምሊን ፌስቱላ ፋውንዴሽን ዋና ስራ አስፈጻሚና የዕለቱ የክብር እንግዳ ካሮሊን አርዲ ለተመራቂዎቹና ለቤተሰቦቻቸው እንኳን ደስ ያላችሁ ብለዋል፡፡

ከ10ኛ ዓመት ክብረ-በዓል ጋር ተያይዞ የኮሌጁን ብሎም የመከላከል ፕሮግራሙን የ10 ዓመታት ጉዞ የሚያሳይ የፎቶ አውደ-ርዕይ ለዕይታ ቀርቧል፡፡ የመከላከል ፕሮግራሙን ለማገዝ መኖሪያ ቤታቸውን ሸጠው 1 ሚሊየን ዶላር ለሐምሊን ፌስቱላ ኢትዮጵያ ለለገሱት አውስትራሊያዊት ሶንያ ፌንተን የምስጋና ምስክር ወረቀት የተበረከተላቸው ሲሆን በመከላከል ፕሮግራሙ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ለተወጡት ለሐምሊን ፌስቱላ ኢትዮጵያ ሰራተኞችም የምስጋና ምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

የጤና ጥበቃ ሚኒስተር ተወካዮችን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች፣ የተለያዩ አገራት አምባሳደሮች፣ የሐምሊን ፌስቱላ ኢትዮጵያ የቦርድና የማናጅመንት አባላት፣ ዓለም አቀፍ የሐምሊን ፌስቱላ ኢትዮጵያ ለጋሾች እንዲሁም የድርጅቱ ሰራተኞች ተሳትፈው ዝግጅቱን አድምቀውታል፡፡



## የ2010 ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ ተከናወነ
- በበጀት ዓመቱ የተሻለ የስራ ክንውን ተመዝግቧል

ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ከሐምሌ 19-20፣ 2010 ዓ.ም. አዲስ አበባ በሚገኘው በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ያከናወነውን ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ በተሳካ ሁኔታ አጠናቀቀ፡፡ በግምገማ መድረኩ የድርጅቱ የማኔጅመንት አባላት፣ የቅርንጫፍ ማዕከላት ኃላፊዎች፣ ሃኪሞች፣ ሜንተሮች፣ ሚድዋይፎችና የመከላከል ባለሙያዎች በድምሩ ከ60 በላይ ተሳታፊዎች ተገኝተዋል፡፡

የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ተጠባባቂ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬ ማሞ በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግራቸው ዓመታዊ ውይይቱ ተቋሙ በበጀት ዓመቱ በየዘርፉ ሲከውን የቆየባቸውን ስራዎች በተናጠልና በጋራ የሚታዩበት በሂደቱም ተሞክሮዎች የሚቀሰሙበት፣ ክፍተቶች የሚለዩበት እንዲሁም በቀጣይ አቅጣጫዎች ላይ የጋራ መግባባት የሚደረስበት መድረክ በመሆኑ የሁሉንም ንቁ ተሳትፎና ትኩረት ይሻል ብለዋል፡፡ ድርጅቱን ወቅቱ ከሚጠይቀው ለውጥ ጋር አብሮ እንዲጓዝ ለማስቻል ቆም ብሎ ስራን የመገምገም አስፈላጊነትን ያነሱት አቶ ተስፋዬ ተሳታፊዎችም ለዚሁ ስኬት



ተዘጋጅተው በመገኘታቸው አመስግነዋል፡፡

በመድረኩ የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ሶስቱ ዋና ፕሮግራሞች ህክምና፣መከላከል፣ ማገገምና መልሶ ማቋቋም ላይ ያተኮሩ ሪፖርቶች በየዘርፉ ኃላፊዎች ቀርበው ውይይት የተደረገባቸው ከመሆኑም ባሻገር የየቅርንጫፍ ማዕከላት ሪፖርቶችም ቀርበውም ተሳታፊው መክሮባቸዋል፡፡



በውይይቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ተሻለና ተመሳሳይ ቅርጽ ያለው ሪፖርት አቀራረብ መመጣቱ፣ በየመሐሉ ዕቅድ እየተከለሰ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት እየተደረገ ያለው ጥረት መጠናከሩና ሐምሊን የሚታወቅበትን ጥራትን ያማከለ አገልግሎት በማስቀጠል ረገድ ያለው ትኩረት በጥንካሬ ከተቀመጡት ዋንኛዎቹ ሲሆኑ በድክመት ደግሞ በባለፈው ዓመት ግምገማ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተወሰኑ ነጥቦች ገሚሶቹ አለመፈፀማቸው፣ የሰውሃብት አስተዳደርና ልማት ክፍል አለመጠናከር፣ ሜንተሮች አካባቢ የሚታይ የስራ ተነሳሽነት መጓደል፣ የቀረቡት ሪፖርቶች እንደ ፊዚዮቴራፒ፣ የስነአዕምሮ፣ የቅርንጫፍ ማዕከላት የማገገምና መልሶ ማቋቋም ተግባራትን አለማካተታቸው፣ ወጪንና ውጤቱን እያመጣጠኑ አለመሄድ ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የድርጅቱ ተጠባባቂ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬ ማሞ የተነሱ አስተዳደራዊ ጥያቄዎችን አንድ በአንድ ምላሽ የሰጡባቸው ከመሆኑም ባሻገር ቀጣይ አቅጣጫዎችንም አመላክተዋል፡፡ ኃላፊው በተጨማሪም የድርጅቱን ፍኖተካርታ አቅርበውም ተሳታፊው በሙሉ መግባባት ተቀብሎት ለተግባራዊነቱ የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበርከት መዘጋጀቱን አሳይቷል፡፡ በመጨረሻም ቅርንጫፍ ማዕከላት የየራሳቸውን የቀጣይ ዓመት ዕቅዳቸውን በጋራ በማቀድ መድረኩ ተጠናቋል፡፡



# የሐምሊን ሚድዋይፎች አሉምናይ ኔትዎርክ ተመሠረተ



በሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅና በግሪንላምፕ አስተባባሪነት “የሐምሊን ሚድዋይፎች አሉምናይ ኔትዎርክ” ቅዳሜ፣ ሐምሌ 21፣ 2010 ዓ.ም በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ተመሰረተ፡፡ በምስረታው ስነ-ስርዓት የኮሌጁ የዘንድሮዎቹን ተመራቂዎች ጨምሮ ከ80 በላይ በስራ ላይ የሚገኙ የሐምሊን ሚድዋይፎች የተገኙ ሲሆን የኔትዎርኩ አባላትም ሆነዋል፡፡

“ለረጅም ጊዜ ስናቅደው የነበርነው እውን ሆኖ በማየቴ እጅግ ተደስቻለሁ፣ እናንተም እንኳን ደስ ያለችሁ” በማለት የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ ዲንና የመከላከል ፕሮግራም ሃላፊ አቶ ዘላለም በለጠ የኔትዎርኩ መመስረት ለሐምሊን ሚድዋይፎች ትልቅ የመማሪያ መድረክ እንደሚሆን ጠቁመዋል፡፡

በምስረታው ስነ-ስርዓት የግሪንላምፕ ፕሬዝዳንት ክርስቲና ብሊቸር በበኩላቸው ንግግር ያደረጉ ሲሆን የአሉምናይ ፅንሰ-ሀሳብና የኔትዎርኩ አስፈላጊነት በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ “አሉምናይ (Alumni) የአንድ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ቀደምት ተማሪዎች ማለት ሲሆን ኔትዎክ ደግሞ በጋራ የሚፈጥሩት ጥምረት ነው፡፡



የሐምሊን ሚድዋይፎች አሉምናይ ኔትዎርክ መመስረት ፋይዳው በዋናነት ለአባላት ቢሆንም ለኮሌጁ ሂድገትና ለአገርቷ ጤና ስርዓት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል" ብለዋል፡፡

የሐምሊን ሚድዋይፎች አሉምናይ ኔትዎርክ ከሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ ተመርቀው በራሳቸው ፍላጎት የመሰረቱት ሲሆን ዓላማውም እነዚህ የኮሌጁ የቀድሞ ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲገናኙ፣ ልምድና እውቀታቸውን እንዲለዋወጡና በኮሌጃቸው የለውጥ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያካትታል፡፡



# አመታዊው የአለም አቀፍ ፓርትነርስ ውይይት መድረክ ተካሄደ

ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ከሰኔ 30 እስከ ሐምሌ 1፣2010 ዓ.ም በሒልተን ኢንተርናሽናል ሆቴል ያካሄደውን አመታዊ የአለም አቀፍ ፓርትነርስ ውይይት መድረክ በተሳካ ሁኔታ አጠናቀቀ፡፡



በድርጅቱ የበላይ ጠባቂ ቦርድ አመራር አባላት በተመራው በዚህ የውይይት መድረክ ከስምንቱ የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ቋሚና የረጅም ጊዜ ለጋሽ ድርጅቶች በተጨማሪ የተቋሙን ተግባራት በከፊል የሚያግዙ ሌሎች ድርጅቶችም ተሳትፈውበታል፡፡

በዶ/ር ፈቃደ አየናቸው፣ የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ሜዲካል ዳይሬክተር አማካኝነት በህክምናው ረገድ ያለውን አመታዊ አፈፃፀም በማቅረብ የጀመረው የውይይቱ የመጀመሪያ ቀን ውሎ የድርጅቱ የመከላከል ዘርፍ፣የማገገምና መልሶ ማቋቋም እንዲሁም የበጀት አጠቃቀም ሪፖርቶች በተከታታይ ቀርበው ተሳታፊው በሰፊው ሲወያይባቸው አምሽቷል፡፡

በአቶ ተስፋዬ ማሞ አማካኝነት በውይይቱ ሁለተኛው ቀን የቀረበው የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ፍኖተ ካርታ በተሳታፊዎች ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኘ ሲሆን ሊደረግበት ስለሚገባቸው ማስተካከያዎችም መድረኩ ተወያይቶ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

ፍኖተ ካርታውን አስመልክቶ የለጋሾቹ ዋነኛ ስጋት ተደርጎ በቀረበው ፕሮጀክቶቹን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ማሰባሰብ ላይ አወያዩ ዶ/ር ኤፍሬም እንዳሉት ገቢ የማሰባሰቡ ስራ ከሀገር ውስጥም ጭምር እንደሚሰራና በሚቀጥለው የበጀት አመት ሪፖርትም ውስጥ እንደሚካተት ቃል ገብተዋል፡፡



# ከጎበኙን እንግዶች አንደበት

“ከሐምሊን ጋር የቆየ ቀረቤታ ነው ያለኝ፡፡ አሜሪካን ሀገር ሳለሁ በየወሩ 10 ዶላር ከገቢዬ እለግስ ነበር፡፡አሁን የሚደንቅ ስራችሁን በአካል ሳይ በምችለው ሁሉ ስራውን ለማገዝ ለራሴ ቃል ገባሁኝ፡፡”



ክብርት ቀዳማዊት እመቤት ወ/ሮ ዝናሽ ታያቸው

“ባጋጣሚ ባለቤቴ አብራኝ ባለመገኘቷ ቅር ብሏታል፡፡ የከበረ ሰላምታዋን ላንቺ [ለዶ/ር ካትሪን] እንዳደርስላትም አጥብቃ ለምናኛለች፡፡ በኢትዮጵያ የአውስትራሊያ አምባሳደር ከሆንኩ አንስቶ ይህን ድንቅ ስራሽን በተደጋጋሚ የጎበኘሁ ቢሆንም ሁልግዜ እንደ አዲስ እደነቃለሁ፡፡ አንቺን ብቻ ሳይሆን አውስትራልያን ለሚያኮራው በጎ ስራሽ ስናመሰግንሽና ስናከብርሽ እንኖራለን፡፡”



አምባሳደር ማርክ ከአውስትራሊያ ፓርላማ አባላት ጋር በጎበኙን ወቅት ለመስራቿ ዶ/ር ካትሪን ከተናገሩት የተወሰደ

## ችግኝ ተከላ በደስታ መንደር
## “አካባቢያችንን እናልማ ፊስቱላን ከአገራችን እናጥፋ”



ቅዳሜ፣ ሐምሌ 21፣ 2010 ዓ.ም ጠዋት የደስታ መንደር ተራራዎች ልክ በዓመቱ እንደገና ችግኞችን በእጆቻቸው በያዙ እንግዶች ተሞልቶ አርፍዷል፡፡ “አካባቢያችንን እናልማ ፊስቱላን ከአገራችን እናጥፋ” የሚል መሪ መልዕክት የተቀመጠለት የዘንድሮው ችግኝ ተከላ ከወትሮው በተለየ በቁጥራቸው በርከት ያሉ ተሳታፊዎችን ከውጭ የስካውት አባላት፣ በጎፈቃደኞች፣ የተለያዩ ድርጅቶች ተወካዮች እንዲሁም ግለሰቦች ከውስጥ ደግሞ በዋናው መስሪያ ቤት፣ በኮሌጅና ደስታመንደር የሚሰሩ ሰራተኞችን ያሳተፈ ነበር፡፡

ችግኝ ተከላውን ያስጀመሩት የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ማገገሚያና መልሶ ማቋቋሚያ ክፍል ኃላፊ ወ/ሮ በለጥሻቸው ታደሰ ድርጅታቸው እንዲሁም የስራ ክፍላቸው የሚያከናውናቸውን ተግባራት ለተሳታፊዎች ባጭሩ ካስተዋወቁ በኋላ በደስታ መንደር የሚከናወነው ችግኝ ተከላ አካባቢን ከመንከባከብ ያለፈ ፊስቱላን ጨምሮ በአገራትን ከወሊድ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለማስወገድ የየድርሻችንን በማበርከት የተቋሙን መስራች ዶ/ር ካትሪንን ራዕይ ለማሳካት ቃል የመግባት ዓላማን ያነገበ ነው ብለዋል፡፡ ይህን የተቀደሰ አላማ

በመደገፍ በቦታው ለተገኙ ተሳታፊዎችም ልባዊ ምስጋናን ወ/ሮ በለጥሻቸው አቅርበዋል፡፡

በችግኝ ተከላው ባጠቃላይ 200 የሚጠጉ ተሳታፊዎች ባብዛኛው ሀገርበቀል ዝርያ ያላቸው ከ2 ሺህ በላይ የዛፍ ችግኞችን ደስታ መንደርንና ኮሌጁን ደግፎ የያዘ በሚመስለው ተራራማ ስፍራ መትከል ተችሏል፡፡ የስካውት አባላት በህብረ-ዝማሬ የታጀበው ተሳትፎ ለዝግጅቱ ድምቀትን የሰጠው ሲሆን በተዘጋጀው የሻይ ቡና ስነ-ስርዓትም ተሳታፊዎች ስለ ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ የበለጠ እንዲያውቁ የሚያስችላቸው የርስ-በርስ ውይይት አድርገዋል፡፡







የሐምሊን ዜና መጽሔት በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ክፍል በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለድርጅቱ ሠራተኞች የሚሰራጭ ነው፡፡

አስተያየት ወይም ለዜና የሚሆኑ ሀሳቦች ካለዎት ያድርሱን፡፡


*ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ*
*ኮሚዩኒኬሽን ክፍል*
*ስልክ፡+251 113 720083*
*ፋክስ፡+251 113 726252*
*ኢሜይል፡enquiries@hamlinfistula.org*
*ዌብ ሳይት፡www.hamlinfistula.org*


Hamlin Fistula Ethiopia

*Designed & Printed by Everest Printers*